# 1. የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት የዴሞክራሲያዊ አንድነት ስኬቶች

እንደሚታወቀው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት እንደመሆኑ መጠን ሀገራችን በኢህአዴግ መሪነትና በህዝብ የተባበረ ክንድ ፍጹም ጸረ ዴሞክራሲያዊ ከሆነዉ ሥርዐት ተላቃ ሥርዓቱ ዳግም ላይመለስ ወደግበአተ መሬት ወርዶዋል። ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የተጎናጸፉትን ዴሞክራሲያዊ አንድነት እያጣጣሙ የማንነታቸው መገለጫ ይሆነውን ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውንና ታሪካቸውን እያበለጸጉ ይገኛሉ።

ዴሞክራሲያችን ከደርግ ውድቀት አንስቶ በነበረው ሂደት በየጊዜው እያደገና እየጎለበተ የመጣ ሲሆን ከ2000 ዓ/ም አዲሱ ሚሊኒየም ወዲህ ደግሞ የበለጠ ጥልቀት እያገኘ የዴሞክራሲ ተቋማትም እየሰፉና ይበልጥ ውጤታማ እየሆኑ መጥተዋል። በመሆኑም በአዲሱ ሚሊኒዬም ከዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ አኳያ ስንቃኝ በዋናነት የምናየዉ ቀደም ስል ተጀምሮ በየጊዜው እድገት እያሳየ የመጣ መሆኑን ታሳቢ ማድርግ ያስፈልጋል፡፡

## 1.1. ኢትዮጵያን ከመበታተን አድኖ የሰላም ዘብ ያደረገ ፌዴራላዊ ሥርዓት

ማንኛውም የፖለቲካ ሃይል የኢትዮጵያን ህልውና ማስቀጠል የሚችለው ያለፉት ስርዓቶች በብሄሮች፣ ብሄረ-ሰቦችና ህዝቦች አያያዝ ላይ የተከተሏቸውን የተሳሳቱ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማስወገድ ለዚህ በሚመጥኑ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን መተካት፣ በብሄሮች፣ ብሄረ-ሰቦችና ህዝቦች መካከል የፈጠሯቸውን ቅራኔዎች ማስወገድ፣ ለዚሁ የሚመጥንና ካለፈው በዓይነቱ የተለየ አስተሳሰብና እምነትን መላበስ፣ አዲሱን አስተሳሰብ የህዝቦች የጋራ አስተሳሰብ እንዲሆን የማያቋርጥ ርብርብ ማድረግ ሲችል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እንደ ሃገር አንድነቷን ጠብቃ እንድትቀጥል ያደረጉና ሕዝቦቿ አብሮነታቸውን በአዲስ ዴሞክራሲያዊ ግንኙነት ለመገንባት የሚያስችላቸው የብዝሃነት አያያዝ

አቋሞች፣ መሰረታዊ የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ የማስፈፀሚያ ህጎችና ተቋማት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

በማንኛውም ሃገር ብዝሃነት የሰላም ጠንቅ የሚሆነው በማንነቶች መካከል እኩልነት ከሌለ፣ ዕኩል የመልማትና የማደግ ዕድል ካጡ፣ በመካከላቸው መተማመን ከሌለ ነው፡፡ በቅድመ-ፌዴራል ኢትዮጵያ የነበረው ሁኔታም ለዚህ ማሳያ ነው፡፡ የፌዴራል ስርዓቱ እነዚህን ችግሮች የሚያስወግድ ህጋዊና ተቋማዊ ስርዓት ፈጥሯል፣ የማንነቶች እኩልነትና እኩል የመልማት ዕድል ተረጋግጧል፡፡ ውስጣዊ ሰላምን በቀጣይነት የማናጋት ዓቅም ያላቸው ጥያቄዎች መሰረታዊ መልስ አግኝተዋል፡፡ በአፈፃፀም ሂደት አልፎ አልፎ የሚታዩ ክፍተቶችም በየጊዜው እየተስተካከሉ እየሄዱ ናቸው፡፡ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የብዝሃነት አያያዝ መሠረታዊ አቋም በተጨባጭ አፈፃፀም ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህ መንፈስ ያልተቃኙ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና አቅጣጫዎች በሃገራችን ሁኔታ ተፈፃሚ መሆን እንደማይችሉ ሕገ-መንግስቱ ዋስትና ሰጥቷል፡፡ በብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች መካከል ያለው ግንኙነት አንዱ የበላይ ሌላው የበታች የሚሆንበት፣ አንዱ የሃገርን አንድነት የማስጠበቅ ሃላፊነት የተጣለበት ሌላው የማይታመን ወይም አጋፋሪ ተደርጎ የሚታይበት ሂደት ያከተመ መሆኑን በተጨባጭ ሂደት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ስርዓቱ የብዝሃነት አያያዝ ሃገራችንን ከመበታተን አደጋ በማውጣት ዴሞክራሲያዊ አንድነት በህዝቦች የጋራ ዕውቀትና ጉልበት መሰረት እንዲይዝ እያደረገ ይገኛል፡፡

በደርግ ውድቀት ዋዜማ የታጠቁ ሃይሎች መብዛት በወቅቱ ከነበረው አለማዊ ሁኔታ ጋር ተዳምሮ ኢትዮጵያን የመበታተን አደጋ እንደተጋረጠባትና ልትድን የምትችልበት አማራጭ የሌላት የመሰላቸው በርካቶች ነበሩ፡፡ በተለይ ደግሞ በ1987 ዓ.ም በፀደቀው ህገ መንግስታችን ውስጥ የአንቀፅ 39 መስፈር ስጋት ያሳደረባቸው ሃይሎችና ሌሎች የግዛት አንድነት አቀንቃኞች የሰላ ትችት ሲሰነዝሩበት ቢከርሙም በአሃዳዊው ስርዓት ከነበረው ሁኔታ እጅግ በተለየ መልኩ ባለፉት አመታት አንድም የመገንጠል ጥያቄ ሳይነሳ በአንድነታችን ፀንተን ቆይተናል፡፡ ይህም ኢትዮጵያውያን ልዩነታቸውን የሚያቻችልና እኩልነታቸው የሚያከብር ስርዓት እስካላቸው ድረስ የመጀመሪያም ሆነ ሁለተኛ አማራጫቸው ዴሞክራሲያዊ አንድነት መሆኑን

ያሳዩበትና ይሄንንም በየጊዜው እያጎለበቱ የሄዱበት ነባራዊ ሁኔታ መፈጠሩን ያሳያል፡፡ ታፍራና ተከብራ ለዘመናት የኖረችን ሃገር ይበታትናታል ብለው የዩጎዝላቪያና ሶቭዮት ህብረት ማስረጃዎችን የሚያቀርቡ ተቃዋሚዎች ወቀሳዎች ጩኸታቸው ዴሞክራሲያዊ አንድነትን በማረጋገጥ ረገድ ስርዓቱ ባስመዘገባቸው ስኬቶች የተነሳ ብዙዎቹ እየተዳከመ መምጣቱን ማየት ይቻላል፡፡

ከግንቦት 1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ባለው ጊዜ የሻዕብያን ወራራ ለመመከት ከተካሄደው የሶስት ዓመታት ጦርነት ውጭ በመሰረቱ ውስጣዊ ሰላሟን አሰጠብቃ የቀጠለች ሃገር ሆናለች፡፡ በሃገራችን የተረጋገጠው ሰላም ለፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ምቹ መሰረት የጣለ ሆኗል፡፡ የውጭ ኢንቨስትመንት ወደ ሃገራችን እንዲጎርፍ ካደረጉ ምክንያቶች አንዱም ይሄው ነው፡፡ ሃገራችን ግጭት በማይለየው የተወሳሰበው የአፍሪካ ቀንድ ውስጥ ሆና እንኳን ከራሷ አልፋም ሌሎች የአፍሪካ ሃገራትንና የአለምን ሰላም ለማገዝ በቀዳሚነት የተሰለፈች ሃገር ሆናለች፡፡

ሀገራችን በተከተለችው ትክክለኛ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በአለም መድረኮች የአየር ንብረት ለውጥን ጨምሮ በተለያዩ አጀንዳዎች የአፍሪካን የተባበረ ድምፅ መወከል የቻለች ሀገር ሆናለች፡፡ በቅርቡም በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ ተለዋጭ አባል ሆና መመረጧ በሌሎች ሀገራት ተቀባይነትና አመኔታ የማግኘቷ ማሳያ ነው፡፡

## 1.2. የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ያረጋገጠ ፌዴራላዊ ሥርዓት

በሀገራችን የመድብለ ፓርቲ ምህዳር ከተፈጠረ ጀምሮ የተመዘገቡ ውጤቶችን ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ከነበረው የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ወጥተን አሁን የብዙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሳትፎ የምናይበት የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ገንብተናል፡፡ አብዛኛው ፓርቲዎች የሚመሩበት አስተሳሰብና ርዕዮተ-ዓለም የተደራጁበት መሰረት ማንነት መሆኑ በተጨባጭ ታይቷል፡፡ እንዲሁም አንዳንዶቹ በኢትዮጵያዊነት ሽፋን የዱሮውን ስርዓት የሚያቀነቅኑ መኖራቸውን በተጨባጭ ማየት ይቻላል፡፡ ሀገራችን በ1987 ዓ.ም ከተካሄደው የመጀመሪያው ሀገራዊ ምርጫ ጀምሮ አምስት አጠቃላይ ሀገራዊ ምርጫዎችን አካሂዳለች፡፡ መላ ኢትዮጵያውያን የስልጣን

ባለቤትነታቸው ማረጋገጫ በሆኑት በእነዚህ ምርጫዎች በመሳተፍ ይበጀኛል የሚሉትን የፖለቲካ ፓርቲ ለስልጣን አብቅተዋል፡፡ በነዚህ ምርጫዎች የተሳተፉ ፓርቲዎች አማራጮቻቸውን በህዝባዊ መድረኮች፣ በሚዲያና ሌሎች የቅስቀሳ አግባቦች ለመራጩ ሕዝብ የሚያደርሱበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ምርጫውን የሚመራ ነፃና ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚ በሕዝቡ ተሳትፎ በየደረጃው እየተዋቀረ የምርጫዎቹን ፍትሃዊነትና ገለልተኝነት ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ ሕዝቡም በምርጫ የሚያደርገው ተሳትፎ በየጊዜው እያደገ መሄዱን የየምርጫዎቹ መረጃዎች በግልፅ ያሳያሉ፡፡

እስካሁን በተደረጉት ምርጫዎች በተለይም በ2002 ከተካሄደው አራተኛው ሀገራዊ ምርጫ ጀምሮ አሁን መንግስትን የሚመራው ገዢ ፓርቲ ኢሕአዴግ እና አጋር ድርጅቶች ሁሉንም የፓርላማ ወንበሮችን በሚባል ደረጃ በመያዙ የተነሳ የአውራ ፓርቲ ስርዓት የሚታይበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በሀገራችን የሚታየው የአውራ ፓርቲ ስርዓት ከዴሞክራሲያዊና ነፃ ምርጫ የመጣ እንዲሁም በንድፈ ሃሳብም የመድብለ ፓርቲ ስርዓት አንዱ መገለጫና በተግባርም በሌሎች ዴሞክራሲያቸው ባደገ ሀገራትም የሚታይ ነው፡፡

የህዝቦች የድርድርና ስምምነት ውጤት የሆነውን ህገ መንግስት ወደ ተግባር የሚለውጡ ተቋማት ተቋቁመው ወደ መሬት ካላወረዱት የፖለቲካ ስርዓቱ በህገ-መንግስት እየተመራ ነው ሊባል አይችልም፡፡ እዚህ ላይ በሃገራችን ብዝሃነትን በማስተናገድ ህብረ-ብሀሔራዊነት ለመገንባት የተቋቋሙ ተቋማትና ብቃታቸውን መዳሰስ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ለማድረግ የተቋቋሙ ተቋማት ከስርዓቱ የእድሜ ጨቅላነት አንፃር ሲመዘኑ አመርቂ ውጤት የተመዘገበባቸው፣ በትክክለኛ የብዝሃነት አያያዝ መንገድ እየተጓዘ መሆኑን ያሳዩ፣ ወደፊት ስርዓቱን ለማጠናከር የሚያስችል ትምህርት የተገኘባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ህገ-መንግስቱን ለማስጠበቅና የስርዓቱን ዓላማዎች ለማስፈፀም የተቋቋሙ ተቋማት እንደሚከተለው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡

### 1.2.1. የጋራ አስተዳደር

ከጋራ አስተዳደር ጋር ተያይዞ የሚነሳው የመጀመሪያ ጥያቄ የአስተሳሰብ፣ የራዕይና የዓላማ ውክልና ነው፡፡ ብዝሃነትን የማስተናገድ ዓላማ ይዞ

የሚመሰረት ፌዴራላዊ ስርዓት የጋራ አስተዳደሩም ብዝሃነትን ለማስተናገድ በሚመጥን መልኩ መመራት አለበት፡፡ በሃገራችን ፌዴላዊ ስርዓት ፌዴራል መንግስት እንደአካል እና የፌዴራል መንግስት ተቋማት በአጠቃላይ የሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦችና የሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የአስተሳሰብ፣ የፍላጐት፣ የራዕይና የዓላማ ውጤት ናቸው፡፡ ተቋሞቹ ሁሉንም የኢትዮጵያ ህዝቦች በእኩል ለማስተዳደር የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ተቋሞቹን ለመምራት የሚሾሙ አስፈፃሚዎች የኢትዮጵያን ዕድገት፣ አብሮነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ኃላፊነት የተሸከሙ ናቸው፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ተቋማት የሚወጡና የሚፈፀሙ ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ወዘተ… ሁሉንም የኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ፍላጎት፣ ራዕይ እና ዓላማ በማሳካት ላይ ይገኛሉ፡፡ የፌዴራል መንግስትን ስልጣን ተገን በማድረግ አንዱን ለመጥቀም ሌላውን ለመጉዳት የሚደረግ እንቅስቃሴ ክልክል ነው፡፡

የጋራ አስተዳደር ሁለተኛው መገለጫ የፖለቲካ ስርዓቱ አፈፃፀም ሚዛናዊነትን ማስጠበቅ ነው፡፡ የሚወጡ ህጎች፣ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ለሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ በአፈፃፀማቸውም ይህንኑ ሚዛናዊነት ማስጠበቅ አለባቸው፡፡ የፌዴራል ስርዓታችን የጋራ አስተዳደር ወሳኝ መገለጫ ይህንን ሚዛናዊነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የዕድገት ዕቅዶች እንደሃገር አንድነትን ለማጠናከር የሚያስችል የህዝቦችና የክልሎች ትስስር እየፈጠሩ ይገኛሉ፡፡ በሁሉም አካባቢዎች ያሉ ህዝቦች እኩል የማደግ ዕድል እየተመቻቸላቸው መጥቷል፡፡ ይህን ዕድል ተመቻችቶ ሲያበቃ በተለያዩ ታሪካዊ ምክንያቶች ዕድሉን ቶሎ መጠቀም የማይችሉ የተለያዩ አካባቢዎችና ህዝቦች በተለየ ትኩረት ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ እስከ አሁን በዚህ ዙሪያ የተገኙ ውጤቶችና ስኬቶች ለወደፊትም በርካታ ትምህርት የተገኘባቸው ናቸው፡፡

ከጋራ አስተዳደር የሚጠበቅ ሶስተኛው ጉዳይ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ውክልናን ይመለከታል፡፡ ብዙውን ጊዜ ስለውክልና ሲነሳ ጎልቶ የሚወጣው ማንነቶች በህግ-አውጪ አካል ስለሚኖራቸው ውክልና ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት በዚህ ዙሪያ አመርቂ የሚባል ርቀት ሄዷል፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በአንድ በኩል ብሄር ብሄረሰብን መነሻ ሳይደረግ በነፃና ግልፅ የምርጫ ስርዓት የሚመረጡ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ የህዝብ

ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ በምርጫ ሊወከሉ የማይችሉ ማንነቶች በቀጥታ ከራሳቸው እንዲወከሉ ተደርጓል፡፡ በሁለቱ መንገዶች ሁሉም የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች በምክር ቤቱ ተወክለዋል፡፡ ሌላው የብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች ውክልና በፌዴሬሽን ምክር ቤት የተረጋገጠው ነው፡፡ እያንዳንዱ የተለየ ማንነት አለው ተብሎ ዕውቅና ያገኘ ማህበረሰብ የህዝብ ብዛቱን መነሻ ሳይደረግ በምክር ቤቱ ውክልና እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

የሃብት ክፍፍል ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ የጋራ አስተዳደር አራተኛው ተልዕኮና መገለጫ ነው፡፡ የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት የየራሳቸው የሃብት ምንጮች አሏቸው፡፡ ነገር ግን በሁሉም ፌዴራል ሃገራት ፌዴራል መንግስት ከሚሰበሰበው ገቢ የተወሰነውን መጠን ለክልሎች በድጎማ መልክ እንደሚሰጥ ይታወቃል፡፡ በሃገራችንም ፌዴራል መንግስት ከራሱ የገቢ ምንጭ፣ ከዕርዳታና ብድር የሚሰበስበውን ገቢ የተወሰነውን መጠን ለክልሎች ድጎማ እየሰጠ መጥቷል፡፡ ይህ ድጎማ ብዝሃነትን ከማስተናገድ አንፃር ያለው አንደምታ ከፍተኛ ነው፡፡ የሃብት ክፍፍሉ አካሄድ በስርዓቱ ላይ ያላቸውን አመኔታ እየጨመረ እንዲመጣ አድርጓል፡፡

አምስተኛው ጉዳይ የቋንቋ፣ ባህል፣ ታሪክ መጠቀምና ማሳደግን ይመለከታል፡፡ እነዚህ የልዩ ማንነት መገለጫዎች ተፈፃሚ የሚሆኑባቸው መንገዶች በተለያዩ ፌዴራል ሃገራት የተለያዩ ልምዶች አሉ፡፡ በሃገራችን አማርኛ ቋንቋ በታሪካዊ አጋጣሚ ብዙ ብሄሮች ብሄረሰቦች የሚግባቡበት በመሆኑ የፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ ሆኗል፡፡ ሌሎች ቋንቋዎች የቋንቋው ባለቤቶች በሚኖሩበት አካባቢና ራስ አስተዳደር የመጠቀም ሕገ-መንግስታዊ መብት ተረጋግጦላቸዋል፡፡ ማንኛውም ዜጋ በራሱ ቋንቋ በፌዴራል ተቋማት አገልግሎት እንዳያገኝ የሚከለክል ሕግ የለም፡፡ ማንኛውም አማርኛ የማይችል ዜጋ በሚችለው ቋንቋ አገልግሎት ሲጠይቅ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ አገልግሎቱን ማግኘት ይችላል፡፡ ብሄሮች ብሄረሰቦች፣ ህዝቦች የራሳቸውን ባህል የማሳደግ ሙሉ መብት ተጎናፅፈዋል፡፡ የእያንዳንዱ ማንነት ባህላዊ መገለጫዎችና ታሪካዊ ቅርሶች እየተሰባሰቡና በያሉበት ጥበቃ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡ እንዳንዶቹም በዩኔስኮ እንዲመዘገቡ የተደረገ ሲሆን ሌሎቹም ለማስመዝገብ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህ ቀሪ ስራዎች

ቢኖሩም የኢትዮጵያ ህዝብ ባህል የሁሉም ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች ህዝቦች ባህሎች ድምር ውጤት መሆኑን እየተረጋገጠ መጥቷል፡፡

ብዙውን ጊዜ የዴሞክራሲ ተቋማት ተብለው የሚወሰዱት ምክር ቤቶች፣ የሰብአዊ መብት እና እንባ ጠባቂ ተቋማት ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት የፖለቲካ ስርዓቱ ዴሞክራሲያዊ ሂደትና አፈፃፀም የመከታተል፣ የዜጎችና ማንነቶች መብቶች ተፈፃሚነት የማረጋገጥና የአፈፀም ችግሮችን እንዲስተካከሉ የማድረግ ሃላፊነት ያላቸው አካላት ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያትም እነዚህ አካላት ከህግ አስፈፃሚው አካል ተለይተውና ነፃነታቸውን ተጠብቀው እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ የሰብአዊ መብት ኮሚሽንና የእንባ ጠባቂ ተቋም ተጠሪነታቸው ለተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የህዝብ የስልጣን ሉዓላዊነት ማሳያ ነው፡፡ የሰብአዊ መብት ኮሚሽንና እንባ ጠባቂ ተቋም ከተቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ የሰሯቸው ስራዎች የብዝሃነት መብቶችን ከማስጠበቅ አንፃር ሲታይ የሚናቅ አይደለም፡፡ በማደግ ላይ ያለ ጨቅላ ፌዴሬሽን በመሆኑ ከልምድና ከአቅም ማነስ ጋር የተያያዙ ውሱንነቶች የሚታዩ በመሆናቸው ተልዕኮዋቸውን የማስፈፀም ብቃታቸው በየጊዜው ለማሻሻል ወደፊት እየተጠናከሩ እንዲሄዱ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

### 1.2.2. የራስ አስተዳደር

የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት ካረጋገጣቸው ተቋማዊ ስርዓቶች አንዱ የራስ አስተዳደር ነው፡፡ ይህ በዋነኛነት ክልሎችን የሚመለከት ሆኖ ከዚህ በተጨማሪ ልዩ ማንነቶችን የሚመለከቱ ዞናዊ፣ ወረዳዊና የቀበሌ አደረጃጀቶችንና ስልጣንና ሃላፊነታቸውን ያካተተ ነው፡፡ የሃገራችን የራስ አስተዳደር የብዝሃነት አያያዝ መገለጫዎች በሚከተለው መልክ ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡

አንደኛ ብዝሀነት በክልል ህገ-መንግስታት የተስተናገደበት መልክ ነው፡፡ የክልሎች ህገ-መንግስታት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት ያረጋገጣቸውን የብዝሃነት መብቶች አካትተው ይዘዋል፡፡ ይህ ሁሉም ክልሎችና ብሄረሰቦች የብዝሃነት መብቶችን በማስጠበቅ ተመሳሳይና ተቀራራቢ አቋምና አፈፃፀም እንዲይዙ በማድረግ በሃገር ደረጃ የተሟላ

የብዝሃነት መብት ጥበቃ ስርዓት እንዲረጋገጥ እና ተቀራራቢ አፈፃፀም እንዲኖር እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የማንኛውም ማንነት አባል ነኝ የሚል ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሁሉም የሃገሪቱ አካባቢዎች ማንነቱ እንደሚከበርለት በማመን ለሁሉም ብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች የሚኖረው አመለካከት ዴሞክራሲያዊ እንዲሆንና በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ አመኔታ እንዲያሳድር የማድረግ አንደምታ አለው፡፡

ሁለተኛው መገለጫ ከአወቃቀርና ውክልና ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሁሉም የክልሎች ምክር ቤቶች በተደራጁበት ክልል ውስጥ የሚገኙትን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ተወካዮች ያቀፉ ናቸው፡፡ እስከ አሁን ባለው ሂደትም በክልል ምክር ቤቶች አልተወከልንም የሚል ጥያቄ ያቀረቡ ማህበረሰቦች የሉም፡፡ እርግጥ ነው ልዩ የማንነት ዕውቅና ይሰጠን የሚል ጥያቄ ያቀረቡና መልስ ያገኙ ህዝቦች አሉ፣ የቀሩትም ቢሆን ስርዓቱ በሚፈቅደው መንገድ ተረጋግጠ መልስ የሚያገኙ ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ማንነቶች በሚገኙበት ክልል ም/ቤት ውስጥ ተወክለው የማህበረሰባቸውን ጥያቄና ፍላጐት እያሰሙና እየታገሉ መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ በክልሎች አስፈፃሚ አካላት ያለው የብዝሃነት ውክልናም ቢሆን በየጊዜው መሻሻል የሚገባቸው ውሱንነቶች ቢኖሩም በመሠረታዊ አስተሳሰቡ ላይ የመመራት እምነት እየጎለበተ መጥቷል፡፡ የክልሎች ቢሮዎች ባለሙያዎች፣ ከፍተኛ አማካሪዎችና የቢሮዎቹ ተሿሚዎች በየክልሉ ከሚገኙ ማንነቶች በቅጥርም ሆነ በሹመት የሚሳተፉባቸው የማንነት መገለጫዎች እየሆኑ መጥተዋል፡፡

አንዳንድ ክልሎች ከብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች መብቶች ጋር የተያያዙ ስልጣንና ሃላፊነቶች ያሏቸው ሁለተኛ ምክር ቤቶች አደራጅተዋል፡፡ በዚህ የሚጠቀሱት የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች ክልል እና የሀረሪ ክልል ናቸው፡፡ የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች ክልል በክልሉ የሚገኙ ማንነቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የተወከሉበት የብሄረሰቦች ምክር ቤት አቋቁሟል፡፡ የምክር ቤቱ ስልጣንና ሃላፊነት ከፌዴሬሽን ምክር ቤት ስልጣንና ተግባራት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ የክልሉን ነባራዊነት የሚገልፅ ይዘት ያለው ነው፡፡ የማንነቶች ተወካዮች የየብሄረሰባቸውን ጥያቄዎች እና ፍላጎቶች በምክር ቤቱ በማንሳት እንዲታወቅ ያደረጋሉ፣ ምክር ቤቱም በሚነሱት

ጥያቄዎች እየተወያየ የጋራ አቋምና የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲያዝባቸው ያደርጋል፡፡

በራስ አስተዳደር ውስጥ ሶስተኛው የብዝሃነት አያያዝ መገለጫ ከባቢያዊ ምክር ቤቶችና አስተዳደሮች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት ዞኖችን፣ ወረዳዎችንና ቀበሌዎችን የማደራጀት ስልጣን የክልሎች ነው፡፡ ይህ የራስ አስተዳደር እስከ ቀበሌ ባለው የመንግስት መዋቅር ድረስ በመውረዱ እነዚህ ከባቢያዊ የስልጣን አካላት ሰፊ የህዝብ ተሳትፎ የሚረጋገጥባቸው የህዝብ የስልጣን ሉአላዊነት ማረጋገጫዎች ሆነዋል፡፡ በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች የሚገኙ ማንነቶች አብዛኞቹ የየራሳቸው ምክር ቤቶችና የአስተዳደር አካላት በዞንና በወረዳ ደረጃ አቋቁመዋል፡፡ እነዚህ ማንነቶች በሰፈሩበትና በሚገኙባቸው አካባቢዎች ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ፡፡ በተመሳሳይ በቤንሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች እንዲሁም በአማራና ትግራይ ክልሎች ማንነቶችን መሰረት ያደረጉ ዞኖችና አስተዳደሮች ተደራጅተው የየራሳቸው ምክር ቤቶችና የአስተዳደር አካላትን በማቋቋም ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ተግባራዊ እያደረጉ ናቸው፡፡ በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮች ይህንኑ ተቋማዊ ስርዓት በመከተል እየተሻሻሉ መምጣታቸው የሃገራችን ፌዴራል ስርዓት የብዝሃነት አያያዝ ልዩ ያደርገዋል፡፡